ውጤት	%
ፈተና	
ማጠቃለያ ፈተና	
ሌሎች	
☐ቅላላ	

Parent's Signature

ሒልሳይድ ትምህርት ቤት

Excel with our support

Central Administrative office (CMC Campus)
Primary Division phone 011-646-69 40
High School Division Phone 011-646-36 88
Lem Campus (Lem Hotel Area)
Primary Division Phone 011-662 42 31/2
KG Campus (Koteba Area)
Kindergarten Division Phone 011- 645 74 44
P.O.Box 21616 Addis Ababa, Ethiopia
Hillside @ ethionet.et

ሙሉ ስም _____ ☐አል - 11 ሴክሽን _____ ☐ኛው ሩብ አመት ማጠቃለያ ፈተና

የት/ት አይነት – አማርኛ የት/ት ዘመን: 2012☐ም መፈተኛ ክፍል _____ የተሰጠው *50 ደቂቃ*

ምንባብ

በጠቅላላ አነጋገር የሚስማሙትና የሚዋደዱት ለመገናኘት፣ የማይዋደዱትና የማይስማሙት ለመለያየት ሲጥሩ፣ ሲግሩ የሚኖሩ መሆናቸው የታወቀ ነው። ነገር ግን ባንዳሩ ጣልቃ እየገቡ የሚያሰናክሉና የሚከለክሉ ልዩ ልዩ ተቃራኒ ሀይሎች ስላሉባቸው ለመገናኘትም ሆነ ለመለያየት ከሚፈልጉት ሁሉ ወደ ሚፈልጉት ግብ ለመድረስ የሚችሉት ሰዎች የመንፈስ ነፃነት፣ የፈቃድ ብርታትና ቆራጥነት ያላቸው ጥቂት ናቸው። የሚበዙት በስልጣን፣ በባህል፣ በልማድና እነሱን በመሳሰሉት ልዩ ልዩ አስገዳጅ ሀይሎች ተገድደው፣ የማይፈልጉትን፣ የሚጠሉትን ኑሮ ተሸክመው እንደተቸገሩ፣ እንዳማረሩ የሚኖሩ ናቸው፣ የሚስማሙት ለመገናኘት የማይስማሙት ለመለያየት ሲፈልጉ፣ ፍላጎታቸው እንዳይፈፀም ጣልቃ እየገቡ የሚከለክሉ አስገዳጅ ሀይሎች ባይኖሩ ኖሮ በቤተሰብ /በባልናሚስት/፣ በማህበር ከዚያም አልፎ በአለም አለመግባባት ወይም ሁከት ባልኖረ ነበር።

ደመቀችና በሻህ የመንፈስ ነፃነት፣ የፈቃድ ብርታትና ቆራጥነት ካላቸው ጥቂት ሰዎች መካከል መሆናቸውን ታሪካቸው ያሳያል። እንዳገሩ ልማድና ባህል፣ የልጆችን የጋብቻ ኑሮ ለመወሰን ሙሉ ስልጣን ያላቸው ወላጆች በመሆናቸው፣ የደመቀች አባት እንኳንስ አብረው መኖር፣ ፊቱን ላንድ አፍታ ማየቱ ለሚያስጠላት ባል ድረው አብራው እንድትኖር ስላስገደዱዋት ባባትዋ ስልጣን፣ በባህሉ፣ በልማዱ፣ በሁሉ ሽፍታ "ባል"
የሚባለው ሁሉ ያን የጠላችው ባልዋን መስሎ ስለታያት ዳግመኛ ባል ላታገባ ምላ በልጅነትዋ ልጅ አዝላ ወደማታውቀው አገር የተሰደደች ነበረች። በተሰደደችበት አገርም ለነፃ ምርጫዋና ለፈቃድዋ ዋጋ ሳይሰጡ የራሳቸውን ፈቃድ ብቻ ለማስፈፀም የተፈታተንዋትን ሁሉ በአጠገብዋ አላስደርስያላች "የነብር አራስ" የተባለ ስም የወጣላት ነበረች።

በሻህም ቢሆን ገና ለጋ ወጣት ሳለ ጀምሮ ለሁሉም የአካልና የመንፈስ ነፃነትና እንደየ ችሎታው ሰርቶ የመኖር መብትን አጥብቆ የሚመኝ ባንዳሩ የግፍ የጭቆናና ያድልዎ ስራ በማንም ላይ ሲሳራ ባየቁጥር
እንደ እግር እሳት የሚያንገበግበውና የሚያመው ነበር። ሁዋላ እየበሰለና እያስተዋለ ሲሄድ የያንዳንዱ ነፃትም ሆነ መብት መታፈንና የግል፣ የጭቆናው ያድልዎው ቀንበር በህዝቡ ላይ መጫን፣ ሁሉም የጠቅላላው ሥራት ዘርፎችና ቅርንጫፎች ስለሆኑ የሁሉም ስራ የሁሉም መሠረት የሆነው ጠቅላላው ስራት
ካልተለወጠ ምንም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃ ሕዝብ የሚገባውን ነፃነት ሆነ መብት ሁሉ ማግኘት ከጭቆና ሁሉ መውጣት እንደማይችል አመነ።

/ሀዲስ አለማየሁ፣ የልምጥ ገጽ 592-593/

መመሪያ ፪. በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ መርጣችሁ መልስ መስጫ ወረቀቱ ላይ አጥቁሩ።

1. ብርታትና ቆራጥነት ያላቸው ጥቂት ናቸው የተባሉት እነ ማን ናቸው?
   ሀ. አብሮ ለመሆንም ሆነ ላለመሆን የሚፈልጉት ናቸው።
   ለ. የሚዋደዱትን እንዳይገናኙ የሚያደርጉት ናቸው።
   ሐ. በስልጣንና በባህል አብረው እንዲሆኑ የተገደዱ ናቸው።
   መ. ለመለያየትና ላለመስማማ ሲጥሩ ሲግሩ የሚታዩት ናቸው።
2. ደመቀች "የነብር እራስ" የተባለችው በምን ምክኒያት ነው?
   ሀ. ልጇን እንደ ነብር እራስ ይዛ በመሰደዷ ነው። ሐ. ሕይወት እንደ አራስ ነብር ስለሆነበት ነው።
   ለ. ያስቸገራትን በቁጣና በንዴት በማባረሯ ነው። መ. ለነፃ ምርጫ ዋና ፈቃዷ ስለ አልተሰጠ ነው።
3. ደመቀች ባል ላለማግባት የማለችበት ምክኒያት ምንድን ነው?
   ሀ. አባቷ ለማትፈልገው ሰው ስለዳሯት ነው።
   ለ. ለፈቃድዋ ዋጋ ስለአልተሰጠ ነው።
   ሐ. ያለ እድሜዋ በማግባቷ በተፈጠረበት ጥላቻ ነው።
   መ. በልጅነት ልጅ በመውለዷ ነው።
4. በደራሲው አመለካከት ወላጆች የልጆችን ጋብቻ የሚወስኑት በምን ምክኒያት ነው?
   ሀ. የማህበረሰቡ ወግና ልማድ በመሆኑ ነው።
   ለ. ልጆችን ተንከባክበው ያሳደጉ በመሆናቸው ነው።
   ሐ. ተገቢ የሆነ የትዳር ጓደኛ ለመምረጥ ባህላዊ ልማድ ስላላቸው ነው።
   መ. ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ስርአት ተፋልሶ የትዳር መሰረት እንዳይጠፋ ነው።
5. የደመቀችና የበሻህን ማንነት የሚያሳየው ምንድን ነው?
   ሀ. የመንፈስ ነፃነት ሐ. ቆራጥነታቸው ነው
   ለ. ታሪካቸው ነው መ. በባህሉ ምክኒያት መበደላቸው ነው
6. በምንባቡ መሠረት ከሚከተለው ውስጥ የትኛው ስህተት ነው?
   ሀ. የሚስማሙና የማይስማሙ ሰዎች የሚደርሱበት ግብ አላቸው
   ለ. የሰዎች ፍላጎት እንዳይፈፀም የሚያግዱ መሰናክሎች በቤተሰቡም በማህበረሰቡም ውስጥ አሉ
   ሐ. ልዩ ልዩ ተቃራኒ ሀይሎች ከግብ ማደናቀፍ ይችላሉ
   መ. የመንፈስ ነፃነት ያላቸው ሰዎች በአስገዳጅ ሀይሎች ይለያያሉ
7. በሻህ በወጣትነቱ የሚመኘው ምን ነበር?
   ሀ. አስተዋይነትና ብልህነት ነበር ሐ. እንደ እግር እሳት የሚያንገበግበውን ጉዳይ ነበር
   ለ. ለሁሉም ሰው ሰርቶ የመኖርን መብት ነበር መ. ሽፍትነትንና የመንፈስ ነፃነትን ነበር
8. የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ሊያጠቃልለው ይችላል?
   ሀ. የሰዎችን ፍላጎት የሚጫኑ ልዩ ሀይሎች አሉ
   ለ. ለመስማማትም ሆነ ላለመስማማት ጥረት ያስፈልጋል
   ሐ. የመንፈስ ቆራጥነት ያስፈልጋል
   መ. ሁከት ምንጩ አለመግባባት ነው
9. የምንባቡ የመጨረሻ አንቀጽ ዋና ትኩረት ምንድን ነው?
   ሀ. የበሻህ እምነትና ምኞት ነው። ሐ. የመንፈስ ነፃነትና ሰርቶ የመኖር መብት ነው።
   ለ. የበሻህ ግፍንና አድልዎን መቃወም ነው። መ. የማስተዋልና የመብሰል ውጤት ነው።
10. ከሚከተሉት ውስጥ የአለመግባባት ምንጭ የተባሉት የትኞቹ ናቸው?
    ሀ. የማይስማሙትና የሚስማሙት ሀይሎች ናቸው።
    ለ. የመንፈስ ቆራጥነትና ነፃነትን የሚያግዱት ሀይሎች ናቸው።
    ሐ. ሰዎች ፍላጎታቸውን እንዳይፈፅሙ የሚከለክሉት ሀይሎች ናቸው።
    መ. ሰዎች ፍላጎታቸውን ለመፈፀም እንዳይተባበሩ የሚያግዱት ናቸው።

መመሪያ ፪. ከዚህ በታች ለቀረቡት ልዩልዩ ጥያቄዎች ተገቢ የምትሉትን መልስ በመምረጥ አሳዩ።

11. ሰውየው ሙልጭ ብሉ ከከሰረ በኋላ ተቸግሮ ሞተ። የሚለውን በሌላ አባባል ብንፅፈው የትኛው ትክክል ነው?
    ሀ. በመክሰሩ ምክንያት ተጎሳቁሎ ሞተ ሐ. በመቸገሩ ሙልጭ ብሎ ከሰረ
    ለ. ሙልጭ ብሎ ስለከሰረ ሞተ መ. ከተቸገረ በኋላ ሙልጭ ብሎ ከሰረ
12. ስለ ክርክር ትክክል የሆነው የቱ ነው?
    ሀ. በተውኔት መልክ ለመድረክ የሚቀርብ መሆኑ
    ለ. በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ ዕይታ ባላቸው ሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ ሙግት ነው።
    ሐ. በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተቃራኒ ዕይታ ባላቸው ሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ ሙግት ነው።
    መ. ሁሉም
13. የክርክር አቀራረብ መመሪያን የሚገልፀው የቱ ነው?
    ሀ. ሃሳባችሁን በተገቢ የአካል እንቅስቃሴዎች ማገዝ፣ ሐ. ሃሳብን ምስጋና በማቅረብ ማጠናቀቅ፣
    ለ. የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ መጠቀም፣ መ. ሁሉም
14. "ክብረት" በሚለው ቃል ውስጥ በቅጥያ ምዕላድ ሊረባ የሚችለው የትኛው ነው?
    ሀ. -ኽኛ ለ. -ኣት ሐ. -ኽት መ. -ኤ
15. "ራስ የሌለው" ለሚለው ፈሊጥ በትርጉም የሚስማማው _____ ነው።
    ሀ. ይሉኝታቢስ ሐ. ሾጣጣ ራስ ሠ. ሀ ና ሐ
    ለ. ይሉኝታ የማያውቅ መ. ሀ ና ለ
16. አይነ-ስጋ የሚለው ፈሊጥ የሚኖረው የትርጉም ፍች የቱ ነው?
    ሀ. በህይወት ለ. በአካል ሐ. በምናብ መ. ሀ ና ሐ ሠ. ሀ ና ለ
17. የአንድ ልቦለድ ጽሁፍ ታሪኩ የማን ሊሆን ይችላል?
    ሀ. የገፀ-ባህሪያቱ ለ. የደራሲው ሐ. የህብረተሰቡ መ. የተደራሲው
18. ጐጆ ወጣ ብለን ትዳር መሰረተ ካልን ጐህ ቀደደ ብለን _____ እንላለን።
    ሀ. ሰው በለ ለ. ልብስ ቀደደ ሐ. የጋብቻ ውል ቀደደ መ. ሌሊቱ ነጋ
19. የአንድን አጭር ልብ ወለድ ባህሪይ የሚገልፀው የትኛው ነው?
    ሀ. ነጠላ ታሪክ ለ. ውስብስብ ታሪክ ሐ. መሳጭ ታሪክ መ. በርካታ መቼት
20. "ሀገራዊ" በዚህ ቃል ውስጥ ወገንን አመልቀች የሆነው ቅጥያ የቱ ነው?
    ሀ. -ዊ ለ. -ራዊ ሐ. -ኣዊ መ. ራዊ-

መመሪያ ፫. ቀጥለው የቀረቡትን የዘይቤ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

21. "ሰውየው ግዝፈቱ የሰማይ ስባሪ ያክላል። ይህ ዓ/ነገር በምን አይነት ዘይቤ የቀረበ ሊሆን ይችላል።
    ሀ. በአነፃፃሪ ለ. ተምሳሌት ሐ. በግነት መ. ምፀት
22. ሆድ ስለሆድ ሲያስብ ሆድ ስለሆድ ሲያልም፣
    አዕምሮ ሲራቆት ህሊና ሲጨልም።
    እግር ለሆድ ሲያስብ ሰው ለሆዱ ሲያድር፣
    ሃሰት እውነት ሆኖ ያሰኛል ድንግርግር። የሚለው ግጥም በምን አይነት ዘይቤ የቀረበ ነው?
    ሀ. ሰውኛ ለ. አያም ሐ. አነፃፃሪ መ. እንቶኔ
23. ስለ ምፀት ዘይቤ ከሚከተሉት ትክክል የሆነው _____ ነው።
    ሀ. ሰውን ማመን ቀብሮ ነው አለች ቀበሮ ሐ. እሱ ነበር ነው
    ለ. ፈጣን ስለሆነ ኤሊ ይቀድማል መ. ፍረጅኝ አንች ምድር
24. "ሰውን ማመን ቀብሮ ነው አለች ቀበሮ" ይህ ዓ/ነገር ለየትኛው ዘይቤ ተመራጭ ነው?
    ሀ. ለሰውኛ ለ. ለአያም ሐ. እንቶኔ መ. ለዋጭ
25. ለአያም ዘይቤ ትክክለኛ መልስ ሊሆን የሚችለው ቀጥሎ ከቀረቡት ውስጥ _____ ነው።
    ሀ. ቤቱ ይነጋገርበት ሐ. ልጁ <u>የብርሃን ቀንዲል</u> ነው።
    ለ. እያነቡ እስክስታ መ. አመስጋኝ እንደዳዊት

መመሪያ ፬. ቀጥሎ ለቀረቡት ልዩልዩ ሰዋሰዋዊ ነክ ጥያቄዎች ተገቢ የሚሆነውን መልስ ምረጥ/ጭ።

26. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የቁጥር አለመስማማት ችግር የሚታይበት የትኛው ነው?
    ሀ. ብረታብረት ለ. ልጆች ሐ. ሴታሴት መ. እናንተ
27. "ከበደ የጭን ቁስል የተሰኘውን ልብወለድ አንብቦ፣ በልብወለዱ ውስጥ የተከሰቱትን ድርጊቶች በቅደም ተከተል ለጓደኞቹ በቃሉ ተረከላቸው።" ከተናገረው/ከተረከላቸው/ የልብ ወለዱን _____ ነው።
    ሀ. ግጭት ለ. ታሪክ ሐ. መልዕክት መ. ጭብጥ
28. ስለ ትውፊት /ፎክሎር/ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
    ሀ. በማህበራዊ አጋጣሚዎች የሚከወን ተግባራትን የሚያጠቃልል
    ለ. ተረቶችን፣ ሃተታ ተፈጥሮዎችንና ድግሞቶችን የሚያጠቃልል
    ሐ. በአነስተኛ ቡድኖች የሚከወን ኪናዊ ተግባቦት መሆኑ
    መ. ሁሉም
29. ሃገረሰባዊ ልማድ ሲባል ምን ለማለት ተፈልጐ ነው?
    ሀ. ማህበረሰቡ በጋራ የሚከናወኑ ናቸው ሐ. በዕምነት ተቋማት በጋራ የሚከውኑት መሆኑ
    ለ. ፌስቲባልና ክብረ በዓላትን የሚጨምር መ. ሁሉም
30. ትውፊት/ፎክሎር/ ስንት ዘርፎች አሉት?
    ሀ. 2 ለ. 3 ሐ. 4 መ. 5

መመሪያ ፭. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ተገቢ የምትሉትን መልስ "እውነት" ተገቢ ካልሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

31. ስነ-ቃል የልዩ ልዩ ቅርጾች ጥቅል መጠሪያ በመሆን ያገለልግላል።
32. ስኬት መሆን የምንፈልገውን ነገር በማድረግና በመካከል ከሚፈጠር ውድቀት መነሳት ነው ማለት ይቻላል።
33. ጊዜና ቦታ ተወስኖለት፣ ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዬች ላይ ሰዎች ሃሳባቸውን የሚለዋወጡበት ውይይት ተብሎ ይጠራል።
34. አለባበስና ንፅህና ጠብቆ መገኘት ከውይይት የዝግጅት ክፍል ይመደባል።
35. በጸሐፊ ተውኔቱ ድራማው ከተፃፈ በኋላ በውስጡ ያሉትን ገፀባህሪያት ስብዕና፣ በውስጣዊ አስተሳሰብ ማንነት የራሳቸው አድርገው በመድረክ የሚተውኑ ተዋንያን ተብለው ይጠራሉ።

መመሪያ ፮. በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ከ "ለ" ጋር ተስማሚ የሆኑትን አዛምዱ።

ሀ	ለ
36. የትውፊት ሌላ ስሙ	ሀ. ተቃራኒ ዕይታ ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ሙግት
37. የተውኔት አላባውያን	ለ. ኮቴቢስ፣ ኮቴው የማይሰማ
38. ግጥም	ሐ. አች፣ ዎች
39. ጸሐፊ ተውኔት	መ. በትንሽ ቃላት ብዙ ማለት
40. ምዕላድ	ሠ. መቼት፣ ጭብጥና ሴራ
41. የፎክሎር ፕሮፌሰር	ረ. ቤን - አሞስ
42. ልብወለድ	ሰ. ፎክሎር
43. ጥገኛ ምዕላድ	ሸ. የድራማውን መሰረታዊ መልክ የሚነድፍ
44. ክርክር	ቀ. ወደ አነስተኛ አሃድ ሊከፈል የማይችል
45. እግረ ሰላቢ	በ. የገሃዱ አለም ነፀብራቅ

መመሪያ ፯. ለሚከተሉት ደረቅ ጥያቄዎች ተገቢ ማብራሪያ ስጧቸው።

46. የክርክር አቀራረብ መመሪያ ከሆኑት ውስጥ 2ቱን ጥቀሱ? /1 ውጤት/
47. "እጅ መንሻ" ለሚለው ፈሊጥ ፍች ፃፉ? /1 ውጤት/
48. ቴአትር ምንድን ነው? ሰፊ ማብራሪያ ፃፉለት? /1 ውጤት/
49. ትውፊት በውስጡ ከሚይዛቸው ነገሮች 3ቱን ጥቀሱ? /1 ውጤት/
50. የውይይት ቅድመ ዝግጅት ከሆኑት ውስጥ 3ቱን ፃፉ? /1 ውጤት/

መልካም ፈተና!

አዘጋጅ :- መ/ር ሞላዬ